THE NILE CRISIS

ግንቦት ፩ ቀን ፪ሺህ ፬ ዓ.ም.

# <u>እናጨናግፋቸው ! ! !</u>

“መላዕክት በዝግታ ሊያልፉበት በሚፈሩት ቦታ ደደቦች/ሞኞች ይንደረደሩበታል!” ይባላል

በኛ ላይ ግን ይህ አይሠራም፦ እንደብዙ ነገር። በኢትዮጵያ ላይ ያለው ጠ. ሚኒስትር ሞኝም ደደብም አይደለምና! መሠሪ፦ ተንኮለኛ፦ ዐውቆ አጥፊ ወዘተ ነው እንጂ።ጥፋትን እንደልማት፦ ማራቆትን እንደማልበስ፦ ማስራብን እንደማጥገብ…አስመስሎ ማቅረብ የሚችል ነው እንጂ!!!

የአባይን ግድብ በተለያዩ ስሞችና ያለፉትን መሪዎች መውቀሻ የቃላት ውዥንብር በማውረድ፦ ራሱን ብቸኛ ያገር ተቆርቋሪ በማስመሰል፦አስጨበጨበ። የሌለውን ጭምር እንዲያዋጣ አስገደደው። ሊያስገኝ ይችላል የሚለውን ጥቅም እየካበ በዚያው አፉ ድሃው ካፉ ነጥሎ እጠቀማለሁ ብሎ የሚያሠራው ግድብ የሚያመነጨውን ኃይል ግማሹን አዎን ግማሹን ለግብጽና ለሱዳን መጠቀሚያ ይኾናል እያለ ሕዝቡ ያዞረበትን ዐዚም(አፍዝ አደንግዝ) ሳያውቅ፡ አሜን- አሜን ብሏል!!

አኹን ሣንቲም መቆጣጠሩን ትተን አገር ወደማዳኑ እንመለስ። ግልገል ጊቤ 3 ን ያለ ጨረታ ሲያሠራ ኬኒያውያን ጉዳት ይደርስብናል፦ አቶ ጠ. ሚ አይደርስባችሁም እሰጥ-አገባ ላይ ኬንያውያን እንደማይጎዳን ለማረጋገጥ የጥናቱን ዝርዝር እንይ ሲሉ፦ “ይኽማ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ መግባት ነው። ይህንንም በምንም ዓይነት አንፈቅድም ተባለ። እሰይ! እሰይ! ለኋላዊነት መቆርቆር!! 1

ግብጾች ስለአባይ ግድብ ጥናት ሲጠይቁ የሉአላዊነት ነገር ሳይነሳ ‘ግድቡ የሁላችንም ጥቅም ነው፤ውሀው አይቀነስም እንዲያውም የተጣራውን ደለል የለሽን ነው የማቀርብላችሁ ቢልም አሻፈረኝ በማለታቸው ካይሮ ድረስ ሄዶ እንዳላችሁ!!! በኹለት ገለለተኞች ባለሚያዎችና ከየባለጉዳዮቹ ኹለት- ኹለት ባለሞያዎች ተመርጠው ይጠና ተባለ።( የድምጽ ሚዛንን የአልጀርስን የባድመን ስምምነት ተብዬውን በማሰብ እንለፈው) እዚህ ላይ  ግብጽና ሱዳን ባለሞያዎች ለመወሰንና በገለልተኞችም ለመስማማት የትዬ-የለሌ ጊዚ ወሰዱ።ያቀዱትን ያውቃሉና።

ያገራቸው ፖለቲካ ወሳኝ ደረጃ ላይ ሲደርስ “የግድቡ መሠራት ጎልውናችንን ስለሚነካ አንስማማም” አሉ፤፡ እዚህ ላይ ቆም ብለን አንዳንድ ኹኔታዎችን እናጢን።

ሀ- ሙባራክ ሥልጣናቸውን እንደሚለቁ በተናገሩ ማግሥት
የአንድ አገር መንግሥት መሪ ካይሮ ገቡ፤፡ ለምን?
የዚች አገር የቀድሞ መሪዎች
- አባይን ከምንጯ ከቅኝ ግዛቶችዋ ለመደባለቅ ጥረው ነበር፦
- ኤርትራ ወደ እናት ኢትዮጵያ ለመመለስ በተቃረበችበት ጊዜ
ምዕራብ ኤርትራን ከሱዳን ሊደባልቁ ሞክረው ነበር
- የታላቋ ሶማሌን ጠንቅ ጠንስሰው ፈጽመውታል
- የታላቋ ትግራይንም ጠንስሠው ውደማስፈጽሙ

ደርሰዋል (ልበል)፦ ሌሎቹን እንተዋቸው

ለ- የግብጽ ወታደራዊ መሪዎች ብዙ ደም ተቃብተዋል
- የጠ.ሚኒስትሩ ምርጫ የግብጽ ወዳጆችና ደጋፊዎች እንደሚፈልጉት ላይኾን ይችላል። ካልኾነ ወታደራዊ መሪዎች ሥልጣን ላይለቅቁ ይችላሉ ይህ የሚያስከትለው የርስ-በርስ ጦርነት የከፋ ሊኾን መቻሉ ልዩ ዕውቀት አይጠይቅም። ታዲያስ!?

'ባንድ ወንጭፍ ኹለት ወፍ!" የሚባለው መፍትሄአቸው ሊኾን አይችልም?? ይህም ማለት፦"የአባይ ግድብ
ለጎልውናችን ጠንቅ ነው።" ባሉት መሠረት ይህን ጠንቅ ለዘለቄታው ማስወገድ ለአገራቸው ሰላምን ማምጣትና ባለውለታ አያደርጋቸውም?? እነሱንም በደም ከመጠየቅ!

ለዚህስ ያለው ቅድመ ዝግጅት ምን ይመስላል??
የግብጽንና የደጋፊዎቿን አገራቸው ውስጥ ያለውን ነካክተናል።

አገራችን ውስጥስ?
ገና የግድቡ ወሬ ሲነሳ አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረ ውጊያቸው በኹለት ግምባሮች እነዚሁም በኤርትራና በሱማሌ በኩል እንደሚኾን ነበር ያሉት።
በኤርትራ በኩል ስለሚባለው ይህ ጸሐፊ እጅግ ግራ ይጋባል።ይህን መተንተን ጊዜ ማባከን ስለሚኾን "አይመጣምን ትተሸ..." በሚለው እንመራ።
በሱማሌ በኩል የተባለው ማደናገሪያና አቅጣጪያ መስጫ ብቻ ይመስለኛል። በአቅጣጪያው ላይ እናተኩር። ግብጾች ካንድ ዓመት በፊት የ3 ቢሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ በምሥራቅ ኢትዮጵያ በይበልጥም አፋር አካባቢ እንዳዋሉ ተነግሯል። 2

የምዕራቡን ነገር ግብጾች አላነሱትም። ለምን ብለው? አጋሮቻቸው ሱዳኖች ምዕራብ ኢትዮጵያን ገፍተው እንደያዙ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም። ምናልባት ለኹሉ ግልጽ ላይኾን የሚችለው ምንያህል የእርሻ፦ ንግድና ኢንዱስትሪ መረብ በተለይ ጎጃም ውስጥ እንደተበተበ ነው። ባጭሩ ከአስፈላጊ በላይ ነው።

አቶ ጠ. ሚ. በኢትዮጵያ ሊኖር ስለሚችለው ጦርነት ሲያወራ 'ግብጾች ብዙ ጊዜ፦የውጭ ርዳትም ጨምረው ኢትዮጵያን ሊወርሩ ሞክረው አልተሳካላቸውም። አኹንም እንደሚሉት ኢትዮጵያ የተከፋፈለች አይደለችም። ቢሞክሩ ውጤታቸው ከቀድሞው አይለይም!' ብሎ ነበር።

የቀድሞው ታሪክ ዕውነት ነው። ጠላትን አገር ውስጥ አስገብተው አልተዋጉምና! በአኹኑ ጊዜ ግን ነጋዴው ቢባል
ገበሬው...መረጃና ወታደር አይደለምን?

በኢትዮጵያችን ውስጥ ያለውን እንለፈውና በዚህ ዓይነት ጦርነት ቢጀመር አገርን በቀጥታ አሳልፎ መስጠት አይኾንም? በተመሳሳይ የተያዘን አገር ማስመለስ ይቻላል? መቼ?
እሥራኤል ከ49 ዓመታት በፊት ከአረቦች የያዘቻቸው በጂ. አይደሉም? እንዲሁም ቱርኮች ከግሪግ ቆጵሮሳውያን የወሰዱት ከ38 ዓመታት በኋላስ በጃቸው አይደለም?
አያምጣውና እንዳያመጣው አፈፍ ብለህ ተነስ/ሽ ያገር ልጅ።እስካሁን ተልፈስፍሰን እወደቅንበት ወድቀናል። አገር በቁማችን አናስወስድ።

እስላም ታማራው፦ አፋር ከጉራጌው ጴንጤው ከጆሀቫው ወዘተ በአንድ ቆመን የግብጽ መንግሥት ተረጋግቶ እስቲቆም ድረስ የተሀድሶ ግድብ የተባለው እንዲቆምና መቆሙም እንዲታወጅ በያለንበት እንተባበር።

አገር ውስጥ ከ 72 ሺህ በላይ የወጣቶች ማህበሮች/ክበቦች እንዳሉ ተነግሯል። እውጭም የኢ.ወጣቶች በሚያበራታ ፍጥነት እየተዘጋጁ ነው

ኹላችንም እየረዳናቸው በ 15 ቀናት ውስጥ በውጭም በውስጥም ተሠልፈን ገዥዎቹ የግድቡ ሥራ ግብጽ የተረጋጋ መንግሥት እስትታገኝ ድረስ ቆሟል"፡ የሚል "እንዲያውጁ እናድርግ። ካላወጁ "ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥን" ያስታውሱ አያጣድፉን።

እስቲ ፖለቲከኞችም ተባበሩና ወጣቶችን ርዱ!!! አትሞቱም

በተስፋ

ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ